# ከእግዚአብሔር ፍቅር

“ ... እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።” (ኢሳ 48 ፥ 17)



God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ E-mail – hello@ethiogodslove.org



www.ethioGodslove.org


## ኃይልና ሥልጣን

ኃይል:- የሚለውን ቃል የአማርኛው የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፥ጥንካሬ ጉልበት፥ብርታት ይለዋል። የእንግሊዝኛውን መዝገበ ቃላት power (ፓዎር) ደግሞ እኛ ስንተረጉመው:-(አንድን ነገር) በሚገባ ለመሥራት ወይም ለማከናወን የሚረዳ ብቃት ወይም ችሎታ፣የሚል ነው። (the ability or capacity to act or perform effectively)

ሥልጣን የሚለውን ቃል ደግሞ በአማርኛው:- በነገር ሁሉ የመምራት፥የመፍረድ፥ የመግዛት ፥ ማንኛውንም ነገር የማድረግ ሙሉ መብት፥ ሲል፣ የእንግሊዝኛውም:- Authority: የማዘዝ፥ ሕግን የማስከበር፥ ትዕዛዛት የማስፈጸም፥ የመወሰንና የመፍረድ ኃይል፥ ይለዋል።

በዚህ መልዕክታችን ኃይልንና ሥልጣንን አስመልክቶ የእግዚአብሔር ቃል ያስተማረንን ልናካፍላችሁ ጌታ መርቶናል።

ከቃሉ እንደምንረዳው፥በጊዜው ኃያል የሚመስሉ ብዙዎች ቢኖሩም የሥልጣን ባለቤት ግን እግዚአብሔር ነው።

“... ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና...” ሮሜ 13፥1

እግዚአብሔር ወልድ የሆነው ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ፥ ልክ እንደ እግዚአብሔር አብ፥ ሥልጣን ሁሉ አለው።

“እየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው:- ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።” ማቴዎስ 28፥18

እግዚአብሔር አብ በሰዎች ላይ የመፍረድን ሥልጣን ለወልድ ሰጥቶታል:-

“የሰው ልጅም ስለ ሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው።” ዮሐንስ ወ/ 5፥27

ሰው ዳግመኛ በሚወለድበት ጊዜ የእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣን፡ ይሰጠዋል:-

“ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።” የዮሐንስ ወንጌል 1፥12

በጌታ በየሱስ አምነው፥ በትምሕርቱ የሚኖሩት ሁሉ ቢጠቀሙበትም፡ ባይጠቀሙበትም፡ የሕይወትና የአገልግሎት ሥልጣን፡ አላቸው:-

“ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው፥ ድውዮችንም ሊፈውሱ፡ አጋንንትንም ሊያወጡ፡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ፤...” ማርቆስ 3፥14-16

ኃይልም:- ልክ እንደ ሥልጣን የጌታ የእግዚአብሔር ነው። ጌታ አምላካችን፡ የኃያላን ኃያልና የጌቶችም ጌታ ስለሆነ እርሱ ሳይፈቅድ ኃይል ሊኖረው የሚችል ማንም የለም። በዚህ መሠረት:-ጌታ በጠላት ኃይላት (በጽድቅ ጠላቶች) ሁሉ ላይ ለአማኞች መንፈሳዊ ሥልጣን ሰጥቶአል። ቃሉ እንዲህ ይላል:-

“እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፤የሚጎዳችሁም ምንም የለም።” ሉቃስ 10፥19

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ክርስቲያን ልክ እንደ ጌታ እየሱስ፥ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ማለት ይችላል። ይቀርላቸዋልም፡

“ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና:- መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው” ዮሐንስ ወ/ 20 ፥ 22 - 23

እግዚአብሔር ለሚወዱትና ለሚከተሉት የሰጠው ኃይል፥ በማቴዎስ 6፥13 “መንግሥት ያንተ ናትና፥ኃይልም ክብርም፡ ለዘለዓለሙ አሜን” የተባለለትን መለኮታዊ ኃይል ነው፤ ጌታ ይክበር። ኃይልንም እንዴት እንደምንቀበል ሲነግረን:-“...ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥...” ይላል በየሐዋ/ሥራ 1፥8

ለመሆኑ ሥልጣን ምንድን ነው? እነሆ፥እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣንን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጎዳችሁም የለም ሲል ምን ማለቱ ነው?

በትላልቅ ከተሞች፥ብዙ ሕዝብ በሚንቀሳቀስባቸው ሰዓቶች፥የትራፊፊክ ፖሊሶች ቆመው:- አደጋ እንዳይፈጠር ሕግ ያስከብራሉ። እነዚህ ፖሊሶች እጃቸውን አንሥተው መኪኖቹ እንዲቆሙ ቢያዙ:- ወዲያው ይቆማሉ። እንደ ዕውነቱ ከሆነ ፖሊሶቹ መኪኖቹን የማቆም ኃይል የላቸውም። ሰባ ኪሎ የሚመዝን አንድ ፖሊስ ያን የሚያክል ኃይለኛ ዚታዎ መኪና በምን አቅሙ ይገታል? በፍጥነትም መኪናና ሰው በምን ይወዳደራሉ? ነገር ግን የፖሊሱ ኃይል ሥልጣኑ ነው። እርሱም ከሚወክለው መንግሥት ሥልጣን የተነሣ ተፈሪነት አለው፡ በሐገሪቱ መንገዶች ሁሉ ላይ የሚመላለሱት ሁሉ፥ እንግዶችም ሳይቀሩ፥የፖሊሱን ሥልጣን ያውቃሉ፤ይታዘዙትማል። ምክንያቱም ሥልጣን የተወካይ ኃይል ነው።

በኤፌሶን 6፥10 “በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ።” ተብሎ የተጻፈውን፥ ብዙ ሰዎች በራሳቸው እንዲበረቱ የሚናገር ይመስላቸዋል። ከዚህም በመነሣት የገዛ ራሳቸውን በሥጋ ያበረታሉ። ብርቱና ጠንካራ ለመባልም የማያደርጉትና የማይሉት የለም። ቃሉ ግን:- “በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ” ነው የሚለው፤ ጌታ ይክበር።

አንድ ፖሊስ አንዱን ትልቅ መኪና በጉልበቱ ለማቆም ሲታገል ብታዩ ምን ትላላችሁ? በጣም አትገረሙም? ከንቱ ድካምስ አይሆንበትም? ነገር ግን ፖሊሱ በጉልበቱ እጅግ ብርቱና በመጠኑም ታላቅ የሆነውን የጭነት መኪና በተሰጠው ሥልጣን በማዘዝ ማቆም ይችላል። ፖሊሱ:- በጉልበቱ ከማንም ቢያንስም እንኳን በሥልጣኑ ግን ኃይለኞችን ሁሉ ጸጥ ማድረግ ይችላል። ምክንያቱም ሥልጣኑን የሰጠው መንግሥት በሕጋዊ ኃይሉ ስለሚደግፈው ነው።

የእግዚአብሔርም ሰው፥ ከአምላክህ ከተሰጠህ ሥልጣን የተነሣ፥ በሴይጣንና በአጋንንት ፊት እጅህን በማንሣት፥ በና ዝሬቱ ጌታ በእየሱስ ክርስቶስ ስም በርትተህ መቆም ትችላለህ። ጠላትህን የሚያቆመው የጌታህ ሥልጣን እንጂ የአንተ ጉልበት ስላልሆነ፥ ድካምህን አትመልከት። በስሙ ሥልጣን ታምነህ ጽና ! ማዳትንም ታያለህ፤ እግዚአብሔር ይመስገን።

ኬኔት ሔገን፥ እአአ በ1942 ዓም በቴክሰስ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ፓስተር በነበሩበት ወቅት፥ከጌታ በቀር፥ለማንም ያልገለጹት ደዌ ነበረባቸው። ፈውስም የሌለው መሳይ ስቃይ ነበር። ፓስተር ኬኔት ግን በጽኑ ከጸለዩ በኋላ በዕምነት ጨክነው ጌታን ለፈውስ ይጠብቁ ነበር፤

በየጊዜው ዕምነታቸው እጅግ ይፈተን ነበር። በሌሊት እንቅልፍ አይወስዳቸውም ነበር። በዚያንም ጊዜ ተነሥተው ሲጸልዩ ያድሩ ነበር። በዚህ ሁኔታ ለስድስት ሳምንታት ያህል እንደተሣቀዩ:- አንድ ቀን እንቅልፍ ሸለብ አደረጋቸው። ወዲያውም ሕልም ያልሙ ጀመር።ሕልሙም ከጌታ ነበረ።

በሕልሙም ከአንድ ወዳጃቸው ጋር በአንድ ሜዳ መሳይ ቦታ፥እያወጉ ይጓዙ ነበር። እየተጓዙም እንዳሉ፥ ወዳጃቸው በድንገት ዞር ብሎ ወደ ኋላው በኃይል ሲፈረጥጥ ያያሉ። ምን ያለው ጉድ ነው በማለት ተገርመው መለስ ሲሉ ፥ ሁለት አንበሶች ወደ እርሳቸው ሲሮጡ ያያሉ። በቁጣና በጭካኔ የተሞላ አስፈሪ አመጣጥ ስለነበረ እርሳቸውም እግሬ አውጪኝ አሉ። ለትንሽ ጊዜም የሚችሉትን ያህል ከሮጡ በኋላ፥ ይህ ሩጫ እንደማያዋጣ ለወዳጃቸው ነገሩትና ለመቆም ወሰኑ።

ወዲያውም በሚያስገርም ቆራጥነት ቀጥ ብለው ቆሙ። ወደ አንበሶቹም ዞረው እየተያዩ ቆሙ። በመጀመሪያ በፍርሐት ትንሽ ተንቀጠቀጡ። ከዚያም:- “በጌታ በእየሱስ ክርስቶስ ስም እቋቋማችኃለሁ፤ከዚህም አልንቀሳቀስም” በማለት ጸንተው ቆሙ። አንበሶቹም እያገሡ ምድሩን የሚያንቀጠቅጡ እየመሰሉ ወደ እርሳቸው ተጣደፉ። ማስፈራታቸውም አስጨናቂ ነበር። ሆኖም፥ አንበሶቹ ልክ ኬኔት ፊት ሲደርሱ ቀጥ ብለው ቆሙ ፤ ወደ እርሳቸውም ትክ ብለው ተመልክተው፤ ልዩ ነገር ያስተዋሉ ይመስል፥ አካባቢውን እንደማሽተት አድርገው፥ ኬኔትን ሳይጎዷቸው ዞረው ወደ መጡበት ተመለሱ ፤ ክብር ለስሙ ይሁን። ወዲያውም ሔገን ከእንቅልፋቸው ሲነቁ በ1ኛ ጴጥሮስ 5፥8-9 ያለው ቃል መጣላቸው። እርሱም:- “በመጠን ኑሩ ንቁም ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤

በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በዕምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት::” ያለው ነው:: ኬኔት ሔገንም ሊያስጨንቃቸው የመጣው ደዌ ከእርሳቸው እንደ ተመለሰ አውቀው በምሥጋና ተቀበሉ:: ከዚያም ደዌ ተፈውሰው ቀሩ:: አያችሁ÷ እኒህ የጌታ ባሪያ በዚያ ሕመም ምክንያት ሞት ቀርቦአቸው ነበር:: ነገር ግን ከብርቱ ጸሎት በኋላ በስሙ ሥልጣን ጸንተው በዕምነት ስለ ቆሙ ÷ የፈውስን ብስራት በሕልም ተቀበሉ::

ስለዚህ ወገኖቼ:- “በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ::” ተብሎ በኤፌሶን 6÷10 እንደ ተጻፈው÷ ጠላቶቻችንን የሚያሸንፍልን÷ በተቀበልነው ሥልጣን የሚሠራ “የኃይሉ ችሎት” ነው፡ እንጂ ከእኛ አይደለም:: የእግዚአብሔር ኃይልና ችሎታው ደግሞ ሁልጊዜም ሁሉን ቻይና ብርቱ ስለ ሆነ:- በዕምነት÷ ሰይፉን በጠላቶቹ ላይ እንደሚያነሣ ተዋጊ ልንጠቀምበት ይገባል:: በእኛ ያለው በዓለም ካለው ይበልጣል ያለው ቃሉ የታመነ ነው:: ቃሉን አምነው ጥቅሙን ለመቀበል ደፍሮ መነሣት ፈተና ቢኖርበትም:- በፈተና የሚጸና ግን ብድራቱን ሳይቀበል አይቀርም፤ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን::

“እነሆ÷ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ÷ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ...” ያለው እርሱ የሥልጣናት ሁሉ ጌታ ነው:: የሥልጣናችን አስፈጻሚና አስከባሪው አምላካችን ጌታ እግዚአብሔር ራሱ ነው:: ይህንን የማይረሳ አማኝ ማንኛውንም ሁኔታና ጠላት ተቋቁሞ በዕምነት መጽናት አይሳነውም እግዚአብሔር ይመስገን::

“ልጆች ሆይ÷እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ ፡ አሸንፋችኋቸውማል ÷ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና::” (1ዮሐ 4÷4) በዓለም ያለው የዚህ ዓለም ገዢ የሆነው የሴይጣን ኃይል ነው:: የጨለማው ዓለም ገዢ÷አለቆችና ሥልጣናት÷በሰማያዊም ስፍራ ያለ የክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ነው:: ሆኖም በእኛ ያለው መንፈስ ቅዱስ÷ ሁሉን የፈጠረውና በሁሉም ላይ ኃይልም ሥልጣንም ያለው ሕያው እግዚአብሔር ነው፤ ስሙ ለዘላለም ይክበር::

ጌታችን እየሱስ በመስቀል ላይ ሞቱና በታላቁ ትንሣዔው በሴይጣን ላይ የተቀዳጀው ዘላለማዊ ድልና ሥልጣን ለሚታመኑበት ሁሉ የሚዋጋ ሥልጣን ነው፤ እግዚአብሔር ይመስገን:: አያችሁ ወገኖች÷ጌታችን አሳልፎ የሰጠን ሥልጣን እኮ÷በማቴዎስ 28÷18 በሰማይና በምድር ተሰጠኝ ያለውን ያንኑ ሥልጣን ነው:: በወንጌል የታዩትን ተዓምራት ሁሉ ያደረገውን÷ ያንኑ ሥልጣን እኮ ነው የሰጠን:: በእውነቱ ሁሉም አማኝ ክርስቶስን በመከተሉ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃይል ቢረዳና ቢለማመድ ዓለም በጌታችን ክብር ፈጥና በተሞላች ነበር::

ይህን ተመልከቱ:- “...እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ÷ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን÷በጸጋ ድናችኋልና÷በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ እየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለ ጠግነት ያሳይ ዘንድ÷ከእርሱ ጋር አስነሣን፡ በክርስቶስ እየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን::” (ኤፌሶን 2÷4-7) ከወደደንና ከሞተልን ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ጋራ ከሞት ወደ ሕይወት ተነሥተናል:: በሰማያዊ ስፍራም ከእርሱ ጋራ አስቀምጦናል:: ገና ወደ ፊት ሳይሆን ከሁለት ሺ ዓመታት በፊት የተረጋገጠ ÷ በንፁሑ የእግዚአብሔር ልጅ ደም የታተመ ሥልጣን ነው:: ይኸውም በዕምነት ለተጠቀሙበት ሁሉ ሲሠራ ታይቶአል:: በዚህም ዘመን በብዙዎቻችን ሕይወት ለመሥራቱ ብዙ ምስክሮች አለን ፤ ስሙ ይክበር:: ወገኔ:- እየሱስ የግል አዳኝህ መሆኑን አምነህ ከተቀበልህና በየዕለቱ በትምሕርቱ የምትኖር ከሆንህ÷ የእርሱ ትንሣዔ ውጤት የሆነው÷ኃይሉና ሥልጣኑ ሁሉ የአንተ ነው ÷ ክብር ለስሙ ይሁን:: ስለዚህ ዕመነው:: ተማመንበት:: ተለማመደውም:: ድሉ የአንተ ነው:: አንቺም::

# መንፈስ ቅዱስና ጸሎት

ዌልሽ በተባለው የእንግሊዝ ሐገር ታላቁ መንፈሳዊ ተሐድሶ (ሪቫይቫል) በሆነበት ወቅት አንድ ወንጌላዊ ነበረ:: እርሱም በእንግሊዝ ከተሞች እየዞረ ሲሰብክ÷ የሰዎች ልብ በቀላሉ ይነካ ነበረ:: በአንድ ስብከቱ ብቻ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ጌታችን እየሱስ ክርስቶስን በአዳኝነቱ አምነው ይቀበሉ ነበረ:: ዝናውም በእንግሊዝ ከተሞችና ባላገሮች ተሰማ:: ይኸውም ዝና ራቅ ባለው ሸለቆአማ ግዛት ለሚኖረው አንድ ወጣት ሰባኪ ደረሰው::

ወጣቱም በስብከቱ ብዙ ሰዎች እንዲድኑ ስለሚመኝ÷ የዚህን ኃይለኛ ስብከት ሚስጢር ለመረዳት÷ ወደ ዌልሽ ከተማ መጓዝ ጀመረ:: ረዥም መንገድም በእግሩ ከተጓዘ በኋላ÷ የተባለው ሰባኪ ከሚኖርበት አንድ ደሳሳ ጎጆ ዘንድ ደረሰ:: ወዲያውም ጊዜ ሳያባክን:- “ወንድሜ ወንጌላዊው ሆይ ! እባክህን ንገረኝ፤ ለመሆኑ ያንን ስብከት ከዬት አገኘኸው?” ሲል ጠየቀው:: ወንጌላዊውም “ና ላሳይህ”አለውና ወጣቱን እየመራ ወደ ጎጆው ውስጥ ገባ:: ወዲያውም በአንድ ጥግ የወለሉ ምንጣፍ የተጐሳቈለበትን ቦታ በጣቱ አመለከተውና:- “ስብከቴን ያገኘሁት ከዚህ ነው” አለው:: ያም እርሱ ሌትና ቀን ተንበርክኮ የሚጸልይበት ቦታ ነበር::

ማብራራቱንም ቀጠለና÷“በዚህች በምታያት ቦታ ተንበርክኬ÷ሰዎች የሚድኑበትን የተቀባ ስብከት መስበክ እንድችል ኃይል ስጠኝ ብዬ÷ ወደ ጌታ አምርሬ አለቀስሁ:: ለረዥም ጊዜ ጸለይሁ:: መንፈቀ ሌሊት ካለፈ በኋላም መልስ አልመጣልኝም:: ጎሕ ቀደደ:: ነጋም:: ይኸውልህ÷ ጉለበቴ በድካም መንቀጥቀጥ በጀመረ ጊዜ ከነጋ በኋላ ያየሰማኸው መልዕክት በኃይል ወረደልኝ:: እኔም ጊዜ ሳላባክን ወጥቼ ሰበክሁ:: ሰዎችም በመንፈስ ቅዱስ ታላቅነት ፊት መቆም ስላልቻሉ መውደቅ ጀመሩ:: አየህ ወጣቱ:- የተቀባ አገልግሎት የብዙ ጸሎት ውጤት ነው:” በማለት ለወጣቱ አስረዳው:: መንፈስ ቅዱስና ጸሎት÷ ጸሎትና መንፈስ ቅዱስ:- ተለያይተው መሄድ የማይሆንላቸው ጥብቅ ወዳጆች ናቸው:: አንዱ ባለበት ሌላኛውም መኖር ይወዳል::

## ደኅንነትን መረዳት

“ደህንነትን መረዳት የዕምነት ውጤት ነው:: ስለዚህ ለማመን መረዳትን ሳይሆን ለመረዳት ዕምነትን መፈለግ አለብህ”

(AUGSTINE c.416)

------------------------------

## እምነት የት ይገኛል?

------------------------------

“እንግዲያውስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው::”

(ወደ ሮሜ ሰዎች 10÷17)

------------------------------

## ከሁሉ አስቀድሞ መስማት የሚገባን የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል?

“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና::”

(የዮሐንስ ወንጌል 3÷16)

ማመን እንኳ አምናለሁ:: ግን ገና ብዙ “መፍጨርጨር” ይቀረኛል::

“ጸጋው (ነፃ ስጦታ) በእምነት አድኖ አችኋልና፤ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤”

(ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2÷8)

------------------------------

ነፃ ስጦታ? ታድያ የኃጢአት ክፋቱ ምኑ ላይ ነው?

የመዳንን ነፃ ስጦታ ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት በመቀበል የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን:: ልጅነትን ከተቀበልን በኋላ በኃጢአት ብንወድቅም በንስሐ ይቅርታ አለልን:: የእግዚአብሔር ልጆች ሆነን ግን በኃጢአት ልንኖር አይቻልም:: “አውቄዋለሁ የሚል ትዕዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው፡ እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም::”

(የዮሐንስ መልእክት 2÷4)

**አንተስ?** እግዚአብሔር የቱን ያህል እንደ ወደደህ ታውቃለህ? በጎና ያማረ ዓላማ ይዞ ለታላቅ በረከት እጆቹን ዘርግቶ እንደሚጠባበቅህስ ታውቃለህ? ጌታ ኢየሱስ እንዲህ ይላል :- “እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል::”

(ዮሐንስ ራዕይ 3÷20)

## የንስሐ ፀሎት

እግዚአብሔር ሆይ ÷ እነሆ የልቤን ደጅ እከፍትልሃለሁ :: ከኃጢአትና ከፍርድ እድን ዘንድ÷በትምሕርቱም ለመኖር ኢየሱስን በጌትነቱ አምኜ እቀበላለሁ:: ከኃጢአት እርቃለሁ:: አንተም በመንግሥትህ ተቀበለኝ:: ስለ ስምህ:: አሜን::

## እየሱስ ጌታ ነው:: ጌታ ይባርክህ/ሽ::